# የሥራ አጥነት ኢንሹራንስ ጥያቄን የማስገባት ደረጃዎች

State of Oregon Employment Department

**ከማመልከትዎ በፊት፦** መረጃ ይሰብስቡ

ለሥራ አጥነት መድን ለመመዝገብ ስምዎን፣የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥርን፣የልደት ቀንዎን እና አድራሻዎን ማቅረብ አለብዎት። የዩኤስ አሜሪካ ዜጋ ካልሆኑ፣ የእርስዎን USCIS ቁጥር፣ A-ቁጥር ወይም I-94 ቁጥር መጠቀም ይችላሉ።

ላለፉት 18 ወራት ሙሉ የስራ ታሪክዎን ማቅረብ አለብዎት። ይህ የአሰሪ ስም፣ የአሰሪ አድራሻ፣ የአሰሪ ስልክ ቁጥሮች እና የቅጥር ቀናትን ይጨምራል።

## ደረጃ 01

### የመጀመሪያ ማመልከቻ ያስገቡ

**በእንቴርኔት** ለሥራ አጥነት መድን ክፍያዎች በ unemployment.oregon.gov ላይ ያመልክቱ።

**የስልክ** ጥሪ ፤ **877-345-3484**።

## ደረጃ 02

### ሳምንታዊ ጥያቄዎችን ያስገቡ

የሥራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ለመጀመር፣ እንዲሁም በየሳምንቱ ጥያቄዎችን ማቅረብ አለብዎት። ያለፈውን ሳምንት ጥያቄ ለማቅረብ እስከ እሁድ ድረስ መጠበቅ አለብዎ።

**በእንቴርኔት** ላይ የአንድ ሳምንት ጥቅማጥቅሞችን በ frances.oregon.gov ይጠይቁ።

**ስልክ፡** የአንድ ሳምንት ጥቅማጥቅሞችን **800-982-8920** በመደወል ይጠይቁ

## ደረጃ 03

### ወደ ሥራ ለመመለስ ዝግጁ ይሁኑ

መሥራት መቻል፣ ለሥራ ዝግጁ መሆን እና ሥራን በንቃት መፈለግ። የስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያገኙ ሰዎች፣

ሥራ ለመፈለግ እና የሥራ ፍለጋቸውን ሂደት መመዝገብ ይፈለግባቸዋል።

# በተደጋግሞ የሚነሱ ጥያቄዎች

### የሥራ አጥነት መድን ( እንሹራንስ) ምንድን ነው?

የሥራ አጥ ኢንሹራንስ ሥራ አጥ ለሆኑ ወይም በራሳቸው ጥፋት ሳይሆን ሰዓታቸው ለተቀነሰባቸው ሰዎች ገንዘብ ይሰጣል። ሳምንታዊ ክፍያዎች በንቃት ሥራ የሚፈልጉትን ሰዎች ይደግፋሉ።

### የሥራ አጥነት ዋስትና ማግኘት እችላለሁ?

ብዙ ሰራተኞች ለስራ አጥነት መድን ብቁ ይሆናሉ፣ አሰሪያቸው ጊዜያዊ ወይም ኮንትራት ሰራተኞች ናቸው ቢልም እንኳ። ባለፉት 18 ወራት ውስጥ የስራ ታሪክ ሊኖርዎት ይገባል፣ እና ሌሎች የደመወዝ መስፈርቶች አሉ። ሰዎች ያገኙትን ጥቅማጥቅሞች ልንሰጣቸው እንድንችል ለሥራ አጥነት መድን እንዲመዘገቡ እናበረታታለን።

### ሳምንታዊ ጥያቄ የማቀርበው መቼ ነው?

ጥቅማጥቅሞችን ማግኘትዎን ለመቀጠል፣ ከመጀመሪያ ጥያቄዎ በተጨማሪ በየሳምንቱ ጥያቄ ማቅረብ ያስፈልግዎታል። አንድ ሳምንት ከእሁድ እስከ ቅዳሜ ነው። ያለፈውን ሳምንት ጥያቄ ለማቅረብ እስከ እሁድ ድረስ መጠበቅ አለብዎት። በዚያ ሳምንት ብሠሩም ሳምንታዊ ጥያቄ ያስገቡ።

### ብሰራስ?

ከ40 ሰዓት በታች ከሰሩ እና ከሳምንታዊ የጥቅማጥቅም መጠን ያነሰ ገቢ ካገኙ አሁንም ለጥቅማጥቅሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በሳምንት ውስጥ የሰሩባቸውን ሰዓቶች ሪፖርት ማድረግዎን ያረጋግጡ። ምንም እንኳን እስካሁን ያልተከፈለዎት ቢሆንም፣ ጠቅላላ ገቢዎን ለእያንዳንዱ ሳምንት ሪፖርት ማድረግ አለብዎት።

### ምን ያህል ማግኘት እችላለሁ?

በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያገኙት መጠን፣ የመጀመሪያ ዓመት ተብሎ የሚጠራው፣ የሳምንታዊ ጥቅማ ጥቅሞችዎን መጠን ይወስናል። ዝቅተኛው እና ከፍተኛው ሳምንታዊ ጥቅማጥቅሞች በህግ ተቀምጠዋል።

**እርዳታ ይፈልጋሉ?**

ይህ መረጃ አስፈላጊ ነው። የኦሬጎን የቅጥር መምሪያ (The Oregon Employment Department, OED) የእኩል እድል ኤጀንሲ ነው። አገልግሎቶቻችንን መጠቀም እንዲችሉ OED ነፃ እገዛን ይሰጣል። አንዳንድ ምሳሌዎች የምልክት ቋንቋ እና የንግግር ቋንቋ አስተርጓሚዎች፣ በሌሎች ቋንቋዎች የተጻፉ ጽሑፎች፣ ትልቅ ህትመት፣ ኦዲዮ እና ሌሎች ቅርጸቶች ናቸው። እገዛ ለማግኘት፣ እባክዎ ወደ unemployment.oregon.gov/am ይሂዱ እና ያግኙን ቅጽ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ ወይም በ 877-345-3484 ይደውሉልን። የTTY ተጠቃሚዎች 711 ይደውላሉ።